የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺህ፲፩ ዓ.ም

ሰንጠረዥ 1፡ የአካዳሚያዊ ሠራተኞች መረጃ 5
ሰንጠረዥ 2፡ የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ የሚያሳይ መረጃ 6
ሰንጠረዥ 3፡ የ2011 ዓ.ም የ1ኛ እና የ2ኛ ዓመት ተማሪዎች ቁጥር 6
ሰንጠረዥ 4፡ መጠነ-ማቋረጥ 6
ሰንጠረዥ 5፡ መጠነ-ስንብት 7
ሰንጠረዥ 6፡ የ2011 ዓ.ም የተከታታይ ትምህርት የዲግሪ ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ 7
ሰንጠረዥ 7: የኤክስቴንሽን ተማሪዎች መጠነ-ማቋረጥና መጠነ-ስንብት 8
ሰንጠረዥ 8፡ የአውት ሶርስ ሠራተኞች ቁጥር 9
ሰንጠረዥ 9፡ በንግድ ሥራ የተሰማሩ የአውትሶርስ ሠራተኞች ቁጥር 9
ሰንጠረዥ 10፡ ጠቅላላ የሠራተኞች ቁጥር 9
ሰንጠረዥ 11፡ የተሰጡ የማህበረሰብ አግልግሎቶች ዝርዝር 23
ሰንጠረዥ 12፡ ዓመታዊ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ንጽጽር 24
ሰንጠረዥ 13፡ የ2011 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት የዕቅድ ክንውን ንጽጽር 29

መግቢያ 3

ክፍል አንድ፡ መሠረታዊ መረጃዎች እና የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት 5

1.1. *መሠረታዊ መረጃዎች* 5

1.2. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት 10

ክፍል ሁለት፡ የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት 14

1.1. አሠራር፣ አደረጃጀት እና መልካም አስተዳደር 14

1.1.1. የልማት ሠራዊት ግንባታ 14

1.1.2. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እና የባለዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነት 15

1.1.3. አሠራርና አደረጃጀትን የሚያሻሽሉ መመሪያዎች 17

1.1.4. የሰው ኃብት አቅምን ማሳደግ 17

1.2. የዩኒቨርስቲውን ገጽታ ግንባታ ማሻሻል 18

1.3. *መደበኛ ትምህርት* 20

1.4. ተከታታይ ትምህርት 20

1.5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት 21

1.6. በጀት አስተዳደርና አጠቃቀም 24

1.7. ቤተ-መጽሐፍትና ስነዳ 25

1.8. የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት 25

1.9. *መንገድ* 26

1.10. የግቢ ውበት፣ ጽዳት፣ ትራንስፖርትና ደህንነት 26

1.11. የተማሪዎች እንቅስቃሴ 27

1.12. የዕቅድ አፈጻጸም ንጽጽር 29

ክፍል ሦስት፡ የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች 34

7.1. አጠቃላይ ሥራዎች 34

7.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች 34

7.2.1. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራ ጎኖች 34

7.2.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ደካማ ጎኖች 36

7.3. ያጋጠሙ ችግሮች 36

7.4. የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች 36

7.5. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 36

አባሪዎች 38

መግቢያ

ትምህርት ብቃት ያለው፣ በራሱ የሚተማመንና ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ለማፍራት እንዲሁም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የሚወስን ማህበረሰብ ለመገንባት እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የተገነቡ ለሰላም መጠበቅ፣ ለሁለንተናዊና ፈጣን ልማት መረጋገጥ እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የድርሻቸውን የሚወጡ ብቁ ዜጎችን የማፍራት ተልዕኮ ያለው ነው፡፡

ትምህርት በሥነ-ጥበብ፣ በማህበራዊ ሣይንስ እንዲሁም በተፈጥሮ ሣይንስና ቴክኖሎጂ የበለፀገ ዜጋ ለመፍጠር፣ የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚጫወተው ሚና የማይተካ ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማስፋፋትና የማበልጸግ ሥራ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲም የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ አካል ሆኖ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 352/2008 ተመስርቷል፡፡

ያለህን ዕምቅ አቅም ለይና ተጠቀም የሚል መሪ ቃል ያለው የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ *በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከትና በሥነ-ምግባር ብቁ የሆኑ ሥራ ፈጣሪ ምሩቃንን ማፍራትና ሀገራዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ያላቸው ሣይንሳዊ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለማህበረሰቡ አገልግሎት መስጠትን* ተልዕኮ አድርጎ ይንቀሳቀሳል፡፡ ዩኒቨርሲቲው *በ2022 ዓ.ም በኢትዮጵያ ተመራጭ በአፍሪካ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ የመሆን* ራዕይንም አንግቧል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በ2010 ዓ.ም ሥራ በጀመረባቸው አራት ኮሌጆች እንዲሁም ከነበሩት 22 የትምህርት ክፍሎች ላይ 2 በመጨመር በ24 የትምህርት ክፍሎች ተደራጅቶ በ193 መምህራን እና 13 ሲኒየር ቴክኒሺያን በአጠቃላይ በ206 አካዳሚያዊ ሠራተኞች የ2011 ዓ.ም የማስተማር ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከአካዳሚያዊ ሠራተኞች በተጨማሪም 222 የአስተዳደር፣ 450 የአውት ሶርስ እና 4 የፕሮጀክት ሠራተኞች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይም 882 ሠራተኞች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከማህበረሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ ሰላሙ የተጠበቀ ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ እና ለምርምር ተግባር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ረገድ እጅግ አመርቂ ጅምር ሥራዎችን በማከናወን ላይ ነው፡፡ የአካባቢው ህብረተሰብ ተቋሙን

እንደራሱ ንብረት የሚያየው በመሆኑ እና የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች ከተማሪዎች ህብረትና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በሠራው የተቀናጀ ሥራ ምክንያት ምንም ዓይነት ግጭትም ሆነ ሌላ የጸጥታ ችግር በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አለመከሰቱ ትልቅ ስኬት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ተመራማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ተገኝተው ሥልጠናዎችን እንዲሰጡ ማድረግ መቻሉ አርዓያነት ያለው ተግባር ሆኖ አልፏል፡፡ ከሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር አጋርነቶችን የመፍጠር ሂደትም ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የተሠራ ሲሆን አመርቂ ውጤቶችም ተገኝተውበታል፡፡

በዚህ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በ2011 በጀት ዓመት በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ተግባራት፣ የግቦች አፈጻጸም፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተሰጡ መፍትሔዎችና በቀጣይም የባለድርሻ አካላትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡

ክፍል አንድ፡ መሠረታዊ መረጃዎች እና የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

1.1. መሠረታዊ መረጃዎች

የተጠቃለሉ የዩኒቨርሲቲው መሠረታዊ መረጃዎች በሚከተሉት ሰንጠረገሮች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የአካዳሚያዊ ሠራተኞች መረጃ

ተ.ቁ	የአካዳሚክ ደረጃ	ኮሌጅ												ድምር			በ%
		ማህበራዊና ሰብዓዊ ሣይንስ			ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ			ግብርና፣ ምግብና ዐየር ንብረት			ተፈጥሮና ቀመር ሣይንስ						
		ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	
1	ፕሮፌሰር	-	-	-	-	-	-	1	0	1	-	-	-	1	0	1	0.52
2	ረዳት ፕሮፌሰር	1	0	1	1	0	1	-	1	1		-		2	1	3	1.55
3	ሌክቸረር	42	8	50	23	3	26	39	10	49	41	15	56	143	36	181	93.8
4	ረዳት ሌክቸረር	-	-	-	-	-	-	-	-	-	1	1	2	1	1	2	1.04
5	ረዳት ምሩቅ I	-	-	-	3	0	3	-	-	-	3	0	3	6	0	6	3.11
ድምር		43	8	51	27	3	30	40	11	51	45	16	61	155	38	193	100
6	ሲኔየር ቴክኒካል ረዳት	-	-	-	-	-	-	5	-	5	8	-	8	13	-	13	-
ጠቅላላ ድምር		43	8	51	27	3	30	45	11	56	53	16	69	168	38	206	

ሰንጠረዥ 2፡ የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ የሚያሳይ መረጃ

የሥራ ክፍል	2ኛ ዲግሪ			የመጀመሪያ ዲግሪ			ዲፕሎማ፣ 10+3 እና level III አቻ			አድቫንስ ዲፕሎማ level IV			10+1፣10+2፣level II አቻ			12ኛ ክፍል እና በታች			ጠቅላላ ድምር		
	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት	1	-	1	11	3	14	-	2	2	1	3	4	-	2	2	-	-	-	13	10	23
አስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት	1	-	1	50	11	61	8	7	15	19	13	32	3	5	8	6	1	7	87	37	124
የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት	-	-	-	23	10	33	3	4	7	10	14	24	1	8	9	-	2	2	37	38	75
ድምር	2	-	2	84	24	108	11	13	24	30	30	60	4	15	19	6	3	9	137	85	222

ሰንጠረዥ 3፡ የ2011 ዓ.ም የ1ኛ እና የ2ኛ ዓመት ተማሪዎች ቁጥር

ተ.ቁ	ኮሌጅ	1ኛ ዓመት ተማሪዎች			2ኛ ዓመት ተማሪዎች			1ኛ እና 2ኛ ዓመት ጠቅላላ ድምር			የሴቶች ድርሻ
		ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	
1	ግብርና፣ ምግብና ዐየር ንብረት ሳይንስ	166	136	302	139	150	289	305	286	591	48.39%
2	ተፈጥሮና ቀመር ሣይንስ	157	100	257	93	104	197	250	204	454	44.93%
3	ማህበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ	149	132	281	83	73	156	232	205	437	46.9%
4	ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ	247	158	405	248	134	382	495	292	787	37.1%
ድምር		**719**	**526**	**1245**	**563**	**461**	**1024**	**1282**	**987**	**2269**	43.5%

ሰንጠረዥ 4፡ የመደበኛ ተማሪዎች መጠነ-ማቋረጥ

ዓ.ም	መጠነ-ማቋረጥ					
	አሳውቀው ያቋረጡ /withdrawal/			ሳያሳውቁ ያቋረጡ /dropout/		
	1ኛ ዓመት	2ኛ ዓመት	**ጠቅላላ**	1ኛ ዓመት	2ኛ ዓመት	**ጠቅላላ**
ወንድ	10	9	19	64	11	75
ሴት	13	-	13	66	5	71
ድምር	23	9	**32**	130	16	**146**
ጠቅላላ ድምር፡ 178						

ሰንጠረዥ 5፡ የመደበኛ ተማሪዎች መጠነ-ስንብት

	መጠነ-ስንብት				
		1ኛ ዓመት		2ኛ ዓመት	
1ኛ ሰሚስተር		በውጤት የተሰናበቱ	የስንብት መጠን	በውጤት የተሰናበቱ	የስንብት መጠን
	ወንድ	24	3.23	9	1.57
	ሴት	53	9.2	20	4.15
	ድምር	77	**5.84**	29	**2.75**
2ኛ ሰሚስተር	ወንድ	59 with 36 Fx	8.27	11 with 5 Fx	1.95
	ሴት	100 with 83 Fx	19.42	22 with 16 Fx	4.8
	ድምር	159 with 118 Fx	**12.95**	33 with 26 Fx	**3.23**

ሰንጠረዥ 6፡ የ2011 ዓ.ም የተከታታይ ትምህርት የዲግሪ ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ

ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ							
		የተመዘገቡ			በመማር ላይ ያሉ (ጠቅላላ)		
ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር
1	አካውንቲንግና ፋይናንስ	103	65	168	95	63	158
2	ኢኮኖሚክስ	55	13	68	30	9	39
3	ማኔጅመንት	176	154	330	105	96	201
ንዑስ ድምር		395	267	662	230	168	398
የማህበራዊና ሰብዓዊ ኮሌጅ							
ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር
1	የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ - የአማርኛ ቋንቋ	70	207	277	51	116	167
2	የእንግሊዝኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ	55	18	73	39	10	49
3	ጂኦግራፊና አካባቢ ጥናት	49	22	71	30	14	44
4	የሥነ-ዜጋ እና ሥነ-ምግባር ጥናት	32	35	67	24	23	47
ንዑስ ድምር		206	282	488	144	163	307
የተፈጥሮና ቀመር ሣይንስ ኮሌጅ							
ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል	ወ	ሴ	ድምር	ወ	ሴ	ድምር

1	ባዮሎጂ	83	59	142	57	35	92
2	ሒሳብ	49	9	58	22	5	27
3	ኮምፒዩተር ሳይንስ	189	73	262	127	40	167
4	ስፖርት ሳይንስ	111	83	194	81	54	135
ንዑስ ድምር		432	224	656	287	134	421
ጠቅላላ ድምር		1033	773	1806	661	465	1126

ሰንጠረዥ 7: የኤክስቴንሽን ተማሪዎች መጠነ-ማቋረጥና መጠነ-ስንብት

	አሳውቀው ያቋረጡ /withdrawal/	ሳያሳውቁ ያቋረጡ /dropout/	በውጤት የተሰናበቱ	የስንብት መጠን
ወንድ	5	312	3	0.45
ሴት	1	254	3	0.65
ድምር	6	566	6	0.53

ሰንጠረዥ 8፡ የአውት ሶርስ ሠራተኞች ቁጥር

ተ.ቁ	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ወንድ	ሴት	ድምር
1	የካምፓስ ፖሊስ (ጥበቃ ሠራተኞች)	83	77	160
2	ጽዳት ሠራተኛ	3	57	60
3	ጽዳትና መስተንግዶ ሠራተኛ	23	45	68
4	ወጥ ቤት	12	46	58
5	ቲከር (የተማሪ ምግብ ተቆጣጣሪ)	6	3	9
6	የተማሪ መኝታ ተቆጣጣሪ (ፕሮክተር)	12	12	24
7	የመኝታ ክፍል ጽዳት	4	42	46
8	እንጀራ ጋጋሪ	2	54	56
9	አትክልተኛ	2	7	9
10	እንጨት ፈላጭ	10	-	10
ጠቅላላድምር		157	343	500

ሰንጠረዥ 9፡ በንግድ ሥራ የተሰማሩ የአውትሶርስ ሠራተኞች ቁጥር

ተ.ቁ	የሥራ ዓይነት	ወንድ	ሴት	ድምር
1	የመዝናኛ ክበብ	8	13	21
2	የፀጉር ቤት /የዉበት ሳሎን/	5	4	9
3	የሱቅ ሠራተኞች	1	1	2
ድምር		14	18	32

በሰንጠረዥ 8 እና 9 እንደሚታየው ከመደበኛ /ቋሚ/ ሠራተኞች በተጨማሪ 482 ለሚሆኑ ግለሰቦች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 10፡ ጠቅላላ የሠራተኞች ቁጥር

	ወንድ	ሴት	ድምር	የሴቶች ድርሻ በ%
የአስተዳደር ሠራተኞች	137	85	222	38.2
የፕሮጀክት ሠራተኞች	4	-	4	0
አውት ሶርስ ሠራተኞች	157	343	500	65.1
መምህራን	155	38	193	19.7
ሲኒየር ቴክኒካል	13	-	13	0
ድምር	466	416	882	47.2

1.2. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

- የ2010 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ሪፖርት ለዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ጸድቋል። ከዚያ በኋላም በሪፖርቱ ላይ ከመምህራን እና ከአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ውይይት ተደርጎ በዳበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ አቅጣጫ ተቀምጧል።
- የዩኒቨርሲቲው የሁለት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ጸድቆ እየተሠራበት ይገኛል። ለሁለት ዓመታት የሆነበት ምክንያትም ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ ጋር እንዲናበብ ለማድረግ ነው። ከዚህ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የተቀዳ የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት፣ ከመምህራንና ከአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ውይይት ተደርጎበት ጸድቋል። ዕቅዱም ለሥራ ክፍሎች ማለትም ለኮሌጆችና ለዳይሬክቶሮች ካስኬድ ተደርጎ የሥራ ክፍሎችም ወደ ፊጻሚ አካላት አውርደዋል።
- የመልካም አስተዳደር ዕቅድ እና የዜጎች የቃል ኪዳን ሠነድ ተዘጋጅቶ ግባራዊ ተደርጓል።
- የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ የ2011 ዓ.ም የውስጥ ዕቅድ አዘጋጅቶ አጽድቋል።
- በበጀት ዓመቱ አካዳሚያዊ ካሌንደር መሠረት በሁሉም ትምህርት ክፍሎች ለአንደኛውና ለሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ለሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች አስፈላጊ ዝግጅቶች ተደርገዋል። በቂ መጽሐፍት ለሌላቸው የትምህርት ዓይነቶችም በግዥና ኮፒ በማድረግም ቁምር እንዲሟሉ ተደርጓል። በኮምፒውተር ላቦራቶሪ ውስጥ የመብራት ዝርጋታ ጥገና ተደርጓል።
- ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተለያዩ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል። ከተሰጡ ሥልጠናዎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተሰጡ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች

ለመምህራን የተሰጡ ሥልጠናዎች፡-

1. ***ጥናትና ምርምር፡-*** ለ24 የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ ለዳይሬክተሮችና ለ12 ሴት መምህራን በአጠቃላይ ለ49 መምህራን ሣይንሳዊ የምርምር አጻጻፍ እንዲሁም ዳታ አያያዝና ትንተና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የምግብ ሣይንስ ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ተፈራ በላቸው እና የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ የ3 ተከታታይ ቀናት ሥልጠና ሰጥተዋል።

2. ***የስታስቲክስና የሪሰርች ሥልጠና፡-*** በካናዳ አገር ዴልሀውስ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪና መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ተሰማ አስታጥቄ ለ60 መምህራንና ለ10 ተማሪዎች የስታቲስቲክስ ሥልጠና የሰጡ ሲሆን በጥናትና ምርምር ዙሪያም የማነቃቂያ ንግግሮችን አድርገዋል፡፡ በሁለተኛ ዙርም የዴልሀውስ ዩኒቨርሲቲ አሰልጣኝ በመመደብ እንዲሁም "አካዳሚክ ውዝአውት ቦርደር" ወጪውን በመሸፈን ለ8 ቀናት ለ86 መምህራን የጥናትና ምርምር ዘዴ አካል በሆነው "Designing Expermnts for Scientific Research" ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህም ለሚቀጥለው ዓመት የሚቀጥል ይሆናል፡፡
3. ***የሰባት ሳይንትስቶች ስልጠና፡-*** እ.ኤ.አ. ጥቅምት 13 ቀን 2018 ዓ.ም ሰባት (7) የተለያዩ የአካዳሚክ ዘርፍ ተመራማሪዎች በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው "Scientfic Consultative Workshop" አካሂደዋል፡፡ በዚህም ለዩኒቨርሲቲው መምህራን ሥልጠና የሰጡ ሲሆን ምርምሮችንም አቅርበዋል፡፡ ይህ የሣይንስ ማህበረሰቡ ዝግጅት፣ እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በሀገሪቱ ተመራጭ ለመሆን የያዘውን ራዕይ ለማሳካት የአካዳሚያዊ ማህበረሰቡን በማነቃቃት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን ከመምህራን ከተገኘው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡ በዕለቱ ወረቀቶች ያቀረቡትና ሥልጠናዎች የሰጡት ሳይንትስቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡
    - **ፕሮፌሰር ብርሃኑ በላይ፡-** የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት
    - **ዶክተር አዛገ ተገኘ፡-** ከዓለም አቀፍ የቁም እንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI)
    - **ዶክተር ወርቅነህ አያሌው፡-** ከዓለም አቀፍ የነፍሳት ሥነ-ባህሪና ሥነ-ምህዳር ማዕከል (ICIPE)
    - **ዶክተር ታደለ ደሴ፡-** ከዓለም አቀፍ የቁም እንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI)
    - **ዶክትር ጌቴ ዘለቀ፡-** የውኃና የመሬት ኃብት ማዕከል ዳይሬክተር (WLRC)፣ አአዩ
    - **ዶክተር ዐይናለም ኃይሌ፡-** ከዓለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢዎች ግብርና ጥናት ማዕከል (ICARDA)
    - **ዶክተር ዳዊት ሰሎሞን፡-** ከዐየር ንብረት ለውጥ፣ ግብርናና ምግብ ዋስትና ጥናት ፕሮግራም (CCAFS)

4. **ሳይንስና ሳይንሳዊ አስተሳሰብ፡-** ፓራሲቶሎጂስት፣ ኢኮሎጂስት እና የጤና መምህር የሆኑት *ፕሮፌር ሽብሩ ተድላ* በሳይንስ ምንነትና በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ዙሪያ የማነቃቂያ ንግግር ለመምህራንና ለተማሪዎች አቅርበዋል፡፡ ከማነቃቂያው ንግግር በተጨማሪ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የአንድ ቀን ሥልጠናም ሰጥተዋል፡፡ ተሳታፊዎችም በፕሮግራሙ እጅግ ደስተኞች እንደሆኑና ትምህርትም እንደቀሰሙ በግብረ መልስ ተገኝቷል፡፡
5. **የፔዳጎጅ ሥልጠና፡-** የክፍል ውስጥ አመራር፣ ተከታታይ ምዘና እና የመምህርነት ሙያ ሥልጠና ያልወሰዱና አዲስ የተቀጠሩ ስድሳ ሦስት (63) ወንዶችና ሀያ ሦስት (23) ሴቶች መምህራን ለ3 ተከታታይ ቀናት ሥልጠናውን ወስደዋል፡፡ ከሥልጠና በኋላ በሁሉም የትምህርት ክፍሎች የካሪክለም መተዋወቅ ሥራም ተካሂዷል፡፡
6. **የአመራር ሥልጠና፡-** ለሠላሳ ስድስት (36) ሴት መምህራን የአንድ ቀን የአመራር ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
7. **የተግባቦት ክህሎት፡-** ለ22 ሴት መምህራን በተግባቦት ክህሎት ዙሪያ የአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
8. **የልምድ ማካፈልና የማነቃቂያ ንግግር፡** የ“Ethiopian Academy of Science” ሴክሬቴሪያትና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይካትሪ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌር አታላይ ዓለም ለዩኒቨርሲቲው መምህራን የህይወት፣ የማስተማር እና የምርምር ልምዳቸውን አቅርበዋል፡፡ ታላቅ ልምድ ያላቸው ፕሮፌሰር አታላይ እ.ኤ.አ የ2019 የHarvard Award in Psychiatric Epidemiology & Biostatistics አሸናፊ ናቸው፡፡

ለተማሪዎች የተሰጡ ሥልጠናዎች፡-

1. **የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥልጠና፡-** 62 ወንድ እና ለ14 ወንድ በድምሩ 76 ተማሪዎች የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያዘጋጀውን ሥልጠና ተሳትፈዋል፡፡
2. **የሥነ-ተዋልዶ እና ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ሥልጠና፡-** በሥነ-ተዋልዶ እና ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ጉዳይ ላይ ለ1218 ተማሪዎች ለ1 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለ97 ፀረ-ኤድስ ክበብ አባላት ለአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ አዲሱን የኤች.አይ.ቪ መመሪያ ኪት በተመለከተ አንድ የክሊኒክ ባለሙያ የሥራ ላይ ሥልጠና ወስዷል፡፡

3. **አካል ጉዳተኞችና ኤች.አይ.ቪ ኤድስ፡-** 3 ሴትና 2 ወንድ በድምሩ 5 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለ3 ቀናት በደብረ-ታቦር ከተማ በአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይ.ቪ ኤድስ እንዲሁም በአካል ጉዳተኞች መብትና ሥርዓተ-ጾታ ዙሪያ ሥልጠና ወስደዋል፡፡
4. **የህይወት ክህሎት ሥልጠና፡-** አዲስ ለገቡ 471 የ1ኛ ዓመት ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት፣ የሠዓት አጠቃቀም፣ የአጠናን ክህሎትና የግጭት አፈታት ለ1 ቀን ሥልጠና ወስደዋል፡፡
5. **ሰላማዊ መማር ማስተማርና የዩኒቨርሲቲው ህግ፡-** ለመላው የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በተቋሙ ህግና ደንብ ዙሪያ ማብራሪያ ተሰጥቶ በአጠቃላይ ዓመቱን እንዴት መማር ማስተማሩ ሰላማዊ ሆኖ ይቀጥላል በሚለው ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡
6. **የማነቃቂያ ንግግሮች፡-** ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ እና ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም ለመምህራን ከሰጡት የማነቃቂያና ልምድ የማካፈል ተግባር በተጨማሪ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችም ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡ የማነቃቂያ ንግግርም አድርገዋል፡፡
7. **የተማሪዎች መማክርት የመስክ ጉብኝት፡-** የተሻለ እንቅስቃሴ የነበራቸው የዘርፍ ኮሚቴ አባላት፣ ም/ተጠሪና ዋና ተጠሪዎችን ያካተተ 46 የተማሪ መማክርት አባላት በ3 ዩኒቨርሲቲዎች በመገኘት የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡

ለአስተዳደር ሠራተኞች የተሰጡ ሥልጠናዎች

1. **አገልግሎት አሰጣጥና የደንበኞች አያያዝ፡-** በዚህ ዙሪያ ለ51 ወንዶችና ለ35 ሴቶች በድምሩ ለ86 የቤተ መጽሐፍት ሠራተኞች ለ2 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
2. **የአመራር ሥልጠና፡-** ለ5 ሴት የአስተዳደር ሠራተኞች የአንድ ቀን የአመራር ሥልጠና ወስደዋል፡፡
3. **በሴቶች መብትና ግዴታዎች፡-** ለ67 ሴት የአስተዳደር ሠራተኞች በሴቶች መብትና ግዴታዎች ዙሪያ የአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
4. **የኤሌክትሮኒክስ ጥገና፡-** የኤሌክትሮኒክስ ጥገና የ2 ወንድ ባለሙያዎችን ክህሎት ለማሳድግ የ15 ቀናት ሙያዊ ስልጠና በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ተከታትለዋል፡፡

5. **የፋይል አከፋፈትና መረጃ አያያዝ፡-** ስለፋይል አከፋፈት እና ስለመረጃ አያያዝ ከፌደራል መንግስት ቤተ-መዛግብት ቢሮ በመጡ ባለሙያዎች ለ10 ወንድ ለ25 ሴት ሠራተኞች የ10 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
6. **BSC፡-** በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ሥርዓት የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ግንዛቤ ለማሳደግ ለ46 ወንድና ለ5 ሴት በድምሩ ለ51 ሠራተኞች (ለሥራ ክፍል ኃላፊዎች፣ ለዳይሬክቶሬቶች እና ለዲኖች) የ3 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከሥልጠናው በኋላም ተጨማሪ ተግባር ተኮር ሥልጠና እየተሰጠ የዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ለየሥራ ክፍሎች ካስኬድ ተደርጓል፡፡
7. **በሲቪል ሰርቪስ መመሪያዎች ዙሪያ የተሰጠ ሥልጠና፡-** ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ የመጡ ባለሙያዎች በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ ዙሪያ ግልጽነት ፈጥረዋል፡፡ ሠራተኛው በተለይም የአስተዳደር ሠራተኛው ጥሩ ግንዛቤውን ያሳደገበት መድረክ ነበር፡፡

ለአውት ሶርስ ሠራተኞች የተሠጠ ሥልጠና

1. **በጸጥታና ደህንነት ዙሪያ የተሰጠ ሥልጠና፡-** አሥር ለሚሆኑ የዩኒቨርሲቲው የጥበቃና ደህንነት አካላት በወንጀል መከላከል፣ በጦር መሳሪያ አያያዝ እና የፍተሻ ደንብ ዙሪያ በ2 ዙር የአምስት ተከታታይ ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ክፍል ሁለት፡ የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት

1.1. አሠራር፣ አደረጃጀት እና መልካም አስተዳደር

1.1.1. የልማት ሠራዊት ግንባታ

በአጠቃላይ በአካዳሚክና በአስተዳደር ዘርፍ 50 የልማት ቡድኖችና 106 የ1ለ5 አደረጃጀቶች አሉ፡፡ የተደራጁ ሠራተኞች ብዛት ወንድ 408 ሴት 296 ድምር 704 ናቸው፡፡ በእነዚህ የሠራተኞች አደረጃጀት ውስጥ ከውይይቶች ተከታታይነት አንጻር ሲታይ የአስተዳደር ሠራተኞች ከአካዳሚክ ሠራተኞች የተሻለ ክንውን አሳይተዋል፡፡

የተማሪዎች የልማት ቡድን ብዛት 47 ሲሆን በዚህ ውስጥ 432 የ1ለ5 አደረጃጀቶች አሉ፡፡ ለተማሪዎች 1ለ5 ሜንተርና የአካዳሚክ አድቫይዘር ተመድቦላቸዋል፡፡ የአቻ ለአቻ የመማማሪያ መድረኮች በመፍጠርም በትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑና ጥሩ ሥነ-ምግባር

ያላቸው ተማሪዎችን ለማፍራት እየተሠራ ነው፡፡ በየሁለት ሳምንቱ ከክፍል ተወካይ ተማሪዎች ጋር በትምህርት ክፍል ደረጃ ውይይት እና በየሳምንቱ ደግሞ የመማር ማስተማር ግምገማ ይካሄዳል፡፡

1.1.2. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እና የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነት

መልካም አስተዳደር፡- አግልግሎቶች የመልካም አስተዳደር እሴቶችንና መርሆዎችን መሠረት አድርገው እየተፈጸሙ ናቸው፡፡ ከሙስና የጸዳ ሥራዎችን ለማከናወንና በጥሩ ሥነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን ለመፍጠር ሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎች፣ የሥራ ላይ ሥነ-ምግባር፣ የሥነ-ምግባር መጽሔቶችን እና የመሳሰሉት በፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የታተሙ ህትመቶች ተሰራጭተዋል፡፡ 14ኛው ዙር የዓለም ፀረ-ሙስና ቀን "ሁለንተናዊ ልማታችንና ሰላማችንን ለማረጋገጥ በሙስና ላይ እንዝመት፤ ጊዜው የተግባር ነው" በሚል መሪ ቃል ተከብሯል፡፡

ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች፡- የፀረ-ጸታዊ ጥቃት (የነጭ ሪቫን) ቀን ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የባህርዳር ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ተማሪዎች እና የሥነ-ምግባር ክበብ አባላት በተገኙበት ተከብሯል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጸታዊ ጥቃቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መሆናቸውን የሚያሳይ መነሻ ጽሑፍ ቀርቦ የፓናል ውይይት ተደርጓል፡፡ ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የአዊ ዞንና የእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉላፊዎች በተገኙበት ተከብሯል፡፡ በመጀመሪያው ወሰነ ትምህር 3.75 እና ከዚያ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ 33 ሴት ተማሪዎችና 4 ነጥብ ያስመዘገቡ 15 ወንድ ተማሪዎች በድምሩ 48 ተማሪዎች ተሸልመዋል፡፡ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ 48 ተማሪዎችን ፎቶና ውጤት የያዘ ባነር ተዘጋጅቶ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተቀምጧል፡፡

ድጋፍን በተመለከተ፡- የገንዘብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ኮሚቴ ተዋቅሮ የገቢ ማስገኛ ስልት መመሪያ በማውጣት ላይ ሲሆን ከተለያዩ አካላት የተገኘ 4,440.00 ብር በዩኒቨርሲቲው አካውንት ገቢ ሆኖ የገንዘብ ችግር ላለባቸው 30 ተማሪዎች ለትራንስፖርት ወጪ ሆኖ ተከፍሏል፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዘንገና ቅርንጫፍ፣ ኢትዮ ቴሌኮም እና ሴት መምህራን ለችግረኞች 6 ደርዘን ደብተር፣ አንድ ፓኮ እስክርቢቶ፣ የንጽህና መስጫ ቁሳቁስ (31 ሳሙናና ሶፍት) ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በአማራ ክልል በተከሰተው የፀጥታ ችግር ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ ጣቢያዎች ለሚገኙ ወገኖች ከዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች ከ5-10% እና በላይ ብር ተሰብስቦ ተልኳል። በዚህም መሠረት ከዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች ብር 193,500.91 ከተቋሙ ብር 300,000 በድምሩ ብር 493,500.91 ለሚመለከተው አካል ተልኳል።

ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል፡- ለአንደኛና ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው በገቡበት ወቅት በአቀባበል ሥነ-ሥርዓት ላይ አሁን ባለው የቫይረሱ አጋላጭ ሁኔታና የስርጭት ሁኔታ ዙሪያ መልዕክት ተላልፏል። ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን የግቢው ማህበረሰብ አባላት ባሉበት በጭውውት፣ በሥነ-ጽሑፍ እና በፓናል ውይይት ተከብሯል።

የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ፡- ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ምርጫ፣ በማደሪያ፣ በመማሪያ ክፍል፣ በላይበራሪ እና ኢንተርኔት አጠቃቀም ዙሪያ የተሻለ አገልግሎትና ቅድሚያ ተሰጥቷል። ለሁለት ዐይነ-ስውራን ተማሪዎች የመንግስትን ተመን መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዳቸው በየወሩ 400.00 ብር እየተሰጣቸው ይገኛል።

የምግብ አገልግሎት፡- የምግብ ጥሬ ዕቃዎችም ሆነ የምግብ ዝግጅቱን የተማሪዎች ተወካዮች እንዲያረጋግጡ በመደረጉ ያለምንም ቅሬታ የምግብ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል። ከዚህ ቀደም በተማሪዎች ምግብ ግብዓቶች ላይ በታየው የጥራት መዋዠቅ ምክንያት ሽሮ፣ በርበሬና እንጀራ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንዲዘጋጅ በመደረጉ በመጠንም ሆነ በጥራት የተሻለ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል።

የመኝታ አገልግሎት፡- ለ2,268 ተማሪዎች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ 464 ዶርሚተሪዎች እና አራት ሕንጻዎች አሉ። በዚህ መሠረት የዶርም ተማሪ ጥምርታው 1፡5 ነው። 3 ቋሚ የተማሪ ማደሪያ ባለአራት ፎቅ ሕንጻዎች 99.76% የግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ። 3ቱ ጊዜያዊ ማደሪያ ዶርሞችና የልብስ ማጠቢያ ክፍል 100% ተገንብተው ተጠናቀዋል። ጊዜያዊ ዶርሚተሪዎች 816 ተማሪዎችን የመያዝ አቅም አላቸው።

የህክምና አገልግሎት፡- 1720 ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ክሊኒክ የሕክምና አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ከዩኒቨርሲቲው ክሊኒክ አቅም በላይ ለሚሆኑ ኬዞች ወደ እንጅባራ ሆስፒታል ሪፈር እየተባሉ ይገኛሉ። በዚህም በእንጅባራ ሆስፒታል 83 ተማሪዎች ህክምና አግኝተዋል።

የዲሲፕሊን ግድፈት፡- ክስ የቀረበባቸው የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ወንድ 32 ሴት 9 ድምር 41 ሲሆኑ በነጻ የተሰናበቱ ወንድ 3፣ ሴት 1፣ በምክር የተናበቱ ወንድ 3 ሴት 2፣

የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ወንድ 3 ሴት 2፣ የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ወንድ 4 ሴት 3፣ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ወንድ 8 ሴት 7፣ ለአንድ ሴሚስተር የተቀጡ ሴት 1 እና ለአንድ ዓመት የተቀጡ ወንድ 4 ናቸው፡፡ ጥፋቶችን ተከታትሎ የእርምት እርምጃ መውሰድ ለሰላማዊ መማር ማስተማር ሂደት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

1.1.3. አሠራርና አደረጃጀትን የሚያሻሽሉ መመሪያዎች

የዩኒቨርሲቲውን አሠራር የሚያሻሽሉ የሚከተሉት የአሠራር መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

1. የአካዳሚያዊ ሠራተኞች ነጻ የትምህርት ዕድል መመሪያ
2. የአስተዳደር ሰራተኞች ነጻ የትምህርት ዕድል መመሪያ
3. የምርምርና ጎትመት ሥራ መመሪያ
4. የማህበረሰብ አገልግሎት መመሪያ
5. የተከታታይ ትምህርት መርኃ ግብር የአሠራር መመሪያ
6. የተማሪዎች የዲሲፕሊን መመሪያ
7. የዝቅተኛና መካከለኛ አመራር የሹመት መመሪያ
8. የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ የአሠራርና የስብሰባ ደንብ

ዩኒቨርሲቲው የአሠራር ሕግና መመሪያን መሠረት አድርጎ በመሥራቱ በፍርድ ቤት የቀረቡ ክሶች የሉም፡፡

1.1.4. የሰው ኃብት አቅምን ማሳደግ

በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርሲቲው 222 የአስተዳደር፣ 450 የአውት ሶርስ፣ 4 የፕሮጀክት ሠራተኞች እንዲሁም 193 መምህራንና 13 ሲኒየር ቴክኒካዊ ረዳቶች በድምሩ 882 ሠራተኞች አሉት፡፡ አስፈላጊ የሆኑ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በማስታወቂያ ኃብዞ በሜሪት ሥርዓት በማወዳደር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውርና በቅጥር ስምሪት ተፈጽሟል፡፡ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ (Job Evaluation and Grading - JEG) የተመዘኑና ደረጃ በወጣላቸው የሥራ መደቦች ላይ በአብዛኛው ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው ቦታ የመመደብ ሥራ ተሰርቷል፡፡ የድልደላ ኮሚቴው በእየምዕራፉ አሠራሩን ግልጽ እያደረገ በመመሪያው መሠረት ምደባ እያደረገ ይገኛል፡፡ የተነሱ ቅሬታዎችም ደረጃ በደረጃ እየታዩና እየተፈቱ ናቸው፡፡ ለ3ኛ ዲግሪ አንድ መምህር በሀገር ውስጥ ትምህርት ላይ የምትገኝ ሲሆን ሌሎች ሦስት (3) መምህራንም የውጭ የ3ኛ ዲግሪ ትምህርት ለመማር በማመልከት ሂደት ላይ

ይገኛሉ፡፡ ከየትምህርት ክፍሉ ሁለት ሁለት መምህራን ለ3ኛ ዲግሪ ለመቀጠል በሂደት ላይ ናቸው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የተለያዩ ሥልጠናዎች እየወሰዱ ሲሆን ከሌሎች ነባር ተቋማትም ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል፡፡

1.2. የዩኒቨርስቲውን ገጽታ ግንባታ ማሻሻል

- አራት የህትመት ውጤቶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሦስት መጽሔቶች ማለትም አዲናስ ዓመታዊ መጽሔት፣ የአዊ መስህብ ኃብቶችን የሚዳስስ መጽሔት እና የሀገር በቀል ጥበባትን የሚያስተዋውቅ መጽሔቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህም መጽሔቶች ለ45 ዩኒቨርሲቲዎች፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር ለሚገኙ 22 መሥሪያ ቤቶች እና ለአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር የዞንና የወረዳ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች፣ በእንጅባራ ከተማ ለሚገኙ ባንኮችና ኢንሹራንሶች፣ ለእንጅባራ ፖሊ ቴክኒክና መምህራን ኮሌጅ እንዲሁም ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ክፍሎች ተሰራጭተዋል፡፡
- ለተለያዩ የዩኒቨርሲቲው የሥራ ክፍሎች የጋዜጣና የመጽሔት ስርጭት ተደርጓል፡፡
- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በአጠቃላይ 10 መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም፡-
  - የትምህርት ፍኖተ ካርታ፣
  - የተማሪዎችን መተዳደሪያ ደንብ ለአዲስ ተማሪዎች ማስተዋወቅ፣
  - ለተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራም፣
  - የዓለም ኤድስ ቀን፣
  - የነጭ ሪቫን ቀን፣
  - ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን፣
  - የሴት ተማሪዎች ሽልማት ፕሮግራም፣
  - ለኤክስቴንሽን ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም፣
  - ለዞን፣ ለወረዳና ለከተማ አስተዳደር አመራሮች ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ መድረክ፣
  - ለሀገር ሽማግሌዎች ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ መድረክ
- በዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴዎች ዙሪያ የተለያዩ ዜናዎችና ማስታወቂያዎች ተሰራጭተዋል፡፡ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ 9 ፕሮግራሞች እንዲሁም በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ማለትም በዌብ ሳይት፣ በፌስ ቡክ፣ በዩቲዩብ፣ እና

በቴሌግራም 150 ዜናዎች ተሰርተዋል፡፡ የማህበራዊ ሚዲያ ተደራሽነትን ለመጨመርና ደንበኞችን ለማብዛት ጥረት እየተደረገም ይገኛል፡፡

- የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ለተማሪዎች ያደረገላቸው ደማቅ አቀባበል የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሰላማዊ መማር ማስተማር ዙሪያ የሴኔት አባላት ከባለድርሻ አካላት ጋር ያደረጉት ውይይት በኢትዮጵያ ራዲዮ ተላልፏል፡፡
- የኤግዚቢሽንና ባህል ማዕከል ተከፍቶ የዩኒቨርሲቲውን የጉዞ ሂደት በሚያሳይ መልኩ ተደራጅቷል፡፡
- ለዘጋቢ ፊልም የሚሆን ስክሪፕት እና በዲጅታል ማስታወቂያ የሚለቀቁ መልዕክቶች ተዘጋጅተዋል፡፡
- ከዩኒቨርሲቲው ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት ወዳጅነት የፈጠሩ 3 የሀገር ውስጥ እና 6 የውጭ በድምሩ 10 ተቋማት አሉ፡፡ እነሱም፡-

  የአገር ውስጥ፡-

  - Alpha Solar and Electrical Solutions
  - Family Guidance Association of Ethiopia (FGAE)
  - Progerss Integerated Community Development Organization (PICDO)

  የውጭ ሀገር፡-

  - Academic without Boarders (Canada)
  - Soka University (Japan)
  - University of Udine (Italy)
  - London South Bank University (LSBU)
  - Cornell University (USA)
  - The Integrated Seed Sector Development Programme (ISSD)
  - Kossoye Development Project (KDP)
  - United States of Agency International Development (USAID)
  - Dalhousie University (Canada)
  - Global Knowledge Exchange Network (London)

1.3. መደበኛ ትምህርት

ዩኒቨርሲቲው የ፭ኛና የ፱ኛ ዓመት 2,268 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በ2012 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹን ተማሪዎች ማስመረቅ ይጀምራል፡፡ በ2010 ዓ.ም እንደተደረገው ሁሉ በዚህም ዓመት የመጀመሪያ ቀን የመጀመሪያ ክፍል የሚለው መርህ በአንደኛውም ሆነ በሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ተፈጻሚ ሆኗል፡፡ ከተመዘገቡ 2,522 ተማሪዎች መካከል 254 ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 21 (0.83%) በሞዝድሮዋል፣ 127 (5%) በድሮፕአውት እና 106 (4.2) በመጠነ-ስንብት ያቋረጡ ናቸው፡፡

ለኮመን ኮርሶች የፈተና ፕሮግራም በማውጣት በሁሉም ኮሌጆች ያሉ መደበኛና ተከታታይ ተማሪዎች በአንድ ቀን እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ በትምህርት ክፍሎች የፈተና ኮሚቴዎችን በማቋቋም ፈተናዎች እንዲገመገሙ ተደርጓል፡፡ በዩኒቨርሲቲው 6 ቤተ-ሙከራዎችን ሴትአፕ ማለትም 3 ለተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ እና 3 ደግሞ ለግብርናና የዐየር ንብረት ሳይንስ ኮሌጆች በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት በማሰራት አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ያልተሟሉትን ከደብረ-ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የሴትአፕ ሥራው በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት በካፒታል በጀት መሠራት የነበረበት ቢሆንም የመማር ማስተማሩን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት እንዲሠራ ተደርጓል፡፡ ይህ በመሆኑም ተማሪዎችን ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በመውሰድ የሚሰጠው ትምህርት መቀነስ ተችሏል፡፡

1.4. ተከታታይ ትምህርት

የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪ ኮሚቴው ከተለያዩ አቻ የትምህርት ተቋማት ማለትም ከጎንደር፣ ከደብረ ታቦርና ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች ተሞክሮ ተወስዷል፡፡ ኮሚቴው የአካባቢውን ማህበረሰብ የትምህርት ፍላጎት ለመለየት አሠድር የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በአዊ ዞንና አጎራባች ቦታዎች ላይ አድርጓል፡፡ ቀጥሎም በመርህ ግብሩ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለዩኒቨርሲቲው ያላቸውን ቀረቤታ /Catchment Area/ መሠረት በማድረግ በአዊና በአጎራባች ዞኖች ማስታወቂያ ተለጥፏል፡፡

የተከታታይ ትምህርት በየትምህርት ክፍሉ የየትምህርት ዓይነት ቅደም ተከተል እና በየወሰነ ትምህርቱ የሚሰጡ ኮርሶችን ከዩኒቨርሲቲው የሴኔት ደንብ ጋር እንዲናበብ ተደርጓል፡፡ በተከታታይ ትምህርት 1000 ተማሪዎችን ለመቀበል ታቅዶ 2414 ተማሪዎች

ተመዝግበዋል፡፡ ከተመዘገቡት ውስጥ ፈተናውን ያለፉ 1806 ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት 1163 ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

የክረምት ትምህርት ለመጀመር የአዋጭነት የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ በሴኔት ከጸደቀ በኋላ በ3017 ያህል ተማሪዎች በዘጠኝ የትምህርት ክፍሎች ትምህር እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው ግቢ ውስጥ ዶርም ይዘው ምግብ ዩኒቨርሲቲው እንዲያቀርብላቸው የሚልፈልጉትንና የማይፈልጉትን በመለየት ዝግጅቶችን አድርጎ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

1.5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት

ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ ሊያተኩርባቸው የሚችሉ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፎችን (Thematic Areas) ለመለየት እንዲቻል ከጎንደርና ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ ተቀስሟል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢውን ህብረተሰብ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ለማስገባት ይቻል ዘንድ ከአዊ ዞን አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጋር የውይይት መድረክ ተካሂዷል፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተሉት ስድስት ዘርፎች የዩኒቨርሲቲው የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት የትኩረት ዘርፎች ሆነው ጸድቀዋል፡፡

1. አካባቢና የዐየር ንብረት ለውጥ (Environment and Climate Change)
2. ምግብ ዋስትናና ኑኖ (Food Security and Livelihood)
3. ትምህርትና ማህበረሰባዊ ሥነ-ልቦና (Education and Psychosocial)
4. ስፖርት፣ ባህልና የቱሪዝም ዕድገት (Sport, Culture and Tourism Development)
5. ሥነ-አስተዳደርና ሥነ-ዜጋ (Politics and Ethics)
6. ሥራ ፈጠራና መዋቅራዊ ለውጥ (Entrepreneurship and Organizational Transformation)

ለምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የሚውል ማጣቀሻ መጽሔቶችና ብሮሸሮች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማት ተሰባስበዋል፡፡

በዚህ ዓመት ለሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች ሠላሳ ሁለት ፕሮፖዛሎች ቀርበው ሃያ አምስት የምርምር አጀንዳዎች ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ 6፣ በማህበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ 4፣ በግብርና፣ ምግብና ዐየር ንብረት ሳይንስ 6፣ እንዲሁም በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ 9 የምርምር ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን የእስካሁን አፈጻጸማቸውም ከ75% በላይ ነው፡፡ የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛሎች ግምገማ የተካሄደው

ከየኮሌጆቹ የተውጣጡ መምህራን፣ ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች እና ከግብርና ምርምር ማዕከል ከመጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ነው።

ከግብርናና ተፈጥሮ ሳይንስ የተውጣጡ አሥር ተመራማሪዎች በአማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በተካሄደው ዓመታዊ ፕሮግራም ላይ በመሳተፍ ፕሮፖዛላቸውን አቅርበው ልምድ ቀስመው ተመልሰዋል። የግብርና ኮሌጅ ምርምሮች በዩኒቨርሲቲው የግምገማ ሥርዓት አልፈው በክልል ምርምር መማክርት ጉባኤም ተገምግመው ያለፉ ናቸው። ይህን ተሞክሮ በመውሰድ ሌሎች ኮሌጆችም በክልል ደረጃ እንዲገመገሙ የአማራ ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም ሀሳቡን ተግባራዊ እንዲያደርግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ከዩኒቨርሲቲው አመርቂ ሥራዎች መካከል ተከታታይ ሴሚናሮች ማካሄድ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው። ሁሉም ኮሌጆች ትምህርት ክፍሎችን በመክፋፈል በየተራ በወር አንድ ጊዜ ፕሮግራም አውጥተውና መምህራንን ደልድለው የተለያዩ ሴሚናሮች እንዲቀርቡ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በአጠቃላይ በዓመቱ ውስጥ በዩኒቨርሲቲው መምህራን 25 ሴሚናሮች የቀረቡ ሲሆን ከኮሌጆች አንጻር ከታየም የተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ 7፣ ግብርና ምግብና ዐየር ንብረት ሳይንስ ኮሌጅ 7፣ ቢዝነዝና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ 6፣ ሰብዓዊና ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ 5 ሴሚናሮች ቀርበዋል። በሴሚናሮቹ ላይ መምህራንና ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን በሚቀርቡት መነሻዎች ላይ ውይይት ያደርጋሉ፤ ይከራከራሉ፤ መረጃዎች ይለዋወጣሉ። ይህ ደግሞ የመምህራንን አካዳሚያዊ ችሎታና ልምድ ከማሳደግ አንጻር ትልቅ ድርሻ ያለው ሲሆን ተማሪዎችም ከክፍል ውጭ ትምህርት የሚቀስሙበት ተጨማሪ መድረክ ሆኖላቸው አላፏል። ከዩኒቨርሲቲው መምህራን በተጨማሪም ተጋባዥ እንግዶች ሴሚናሮችን ያቀረቡ ሲሆን ለአብነትም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

1. የጅማ ዩኒቨርሲቲ የመረጃና ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር ግሩም ኩተማ “አይሲቲ እና ከፍተኛ ትምህርት” በሚል ርዕስ፤
2. በአሜሪካ ሀገር የፍሎሪዳ ስቴት ዩኒቨርሲቲ መምህርና የኬሚስትሪ ላብ ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር ሰለሞን ተክሉ “Integrating Green Chemistry into Organic Chemistry Curriculum” በሚል ርዕስ፤
3. የለሲ አካዳሚ ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ኃብታሙ መለሰ በኤሌክትሮኒክስ ትምህርት /e-learning/ ዙሪያ፤

ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ስንመጣ ሠላሳ አራት ፕሮፖዛሎች ቀርበው ሃያዎቹ ጸድቀዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለልማት ተነሽ አርሶ አደሮች ሥልጠና መስጠትንም የሚያካትት ነው፡፡ ለተለያዩ የአካባቢው ማህበረሰብ አካላትም ልዩ ልዩ ድጋፍ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ የማህበረሰብ አገልግሎት ክንውኖች ዝርዝም በሰንጠረዥ 8 እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 11፡ የተሰጡ የማህበረሰብ አግልግሎቶች ዝርዝር

ተ.ቁ	የድጋፍና ሥልጠናው ርዕስ	የስልጠናው ቦታ	ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ	የሰልጣኞች ብዛት		
				ወ	ሴ	ድ
1	የአዊ ድጋግ (ጎንጥላ) ስልጠና	አዘና	10 ቀናት	10	-	10
2	የምልክት ቋንቋ ስልጠና	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	8 ቀናት	20	7	27
3	የወንጀል ምርመራ የሥነ-ሥርዓት ሂደት፣ አተገባበርና የፍትህ አካላት ሙያዊ ሥነ-ምግባር	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	4 ቀናት	30	8	38
4	Life Skill Training: The Case of Awi Zone Preparatory School Counselors and Students	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	3 ቀናት	14	15	29
5	Capacitating Hotel Owners and Employees on Core Hospitality Issues	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	5 ቀናት	6	6	12
6	Book Keeping and Financial Management	ዳንግላ	5 ቀናት	10	2	12
7	Capacitating Hotel Owners and Employees on Core Hospitality Issues	ቻግኒ	5 ቀናት	12	6	18
8	Basic Computer Skills, Computer Hardware Maintenance and Networking, Database and File Management System Training for Secretaries, Sector ICT Experts, High School ICT Teacher and Unemployed TVET/University Graduate and Different Areas in Awi Zone	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	5 ቀናት	3	17	20
9	የአመራር ክህሎት ስልጠና	ዳንግላ	6 ቀናት	115	24	139
10	The Integrated Seed Sector Development Programme (ISSD) Project Training	አዲስቅዳም	2 ቀናት	8	2	10
11	በግብይት፣ እሴት ሰንሰለትና የገበያ ትስስር	እንጅባራ	1 ቀን	20	58	78

	ጽንሰ-ሀሳብና በግብይት ውስጥ ያሉ ማነቆዎችና መፍትሄዎቻቸው					
ድምር				236	139	396

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው Human Bridge ከተባለ ድርጅት እና ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለግምጃ ቤት ሆስፒታል እስከ 8.5 ሚሊዮን እንዲሁም ለቻግኒ ሆስፒታል እስከ 6.5 ሚሊዮን የሚያወጡ የለያዩ የህክምና ዕቃዎች ድጋፍ አድርጓል፡፡

1.6. በጀት አስተዳደርና አጠቃቀም

የ2011 ዓ.ም በጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በግንዘብና ትብብር ሚኒስቴር 150,700,000 (አንድ መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ) ብር ተፈቅዷል፡፡ ተጨማሪ በጀት 19,194,400.00 ብር ተፈቅዶ የዓመቱ በጀት በድምሩ 169,894,400.00 ብር ሲሆን ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም 169,856,379.08 ብር (99.98%) ነው (ሰንጠረዥ 9ን ይመልከቱ)፡፡ ይህ አፈጻጸም ውጤት ሊገኝ የቻለው የግዥ ሂደቱ በበጀት ዓመቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ በመከናወኑና ተከታታይ የግዥ ግምገማ በመካሄዱ ምክንያት ነው፡፡

ሰንጠረዥ 12፡ ዓመታዊ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ንጽጽር

ተ.ቁ	ፕሮግራም	ለ2011 በጀት ዓመት ተስተካክሎ የተመደበ በጀት (ዕቅድ)	ዓመታዊ አፈጻጸም	
			በአሃዝ	በመቶኛ
1	ለሥራ አመራርና አስተዳደር	84,948,342.00	84,936,758.37	99.98%
2	መማር ማስተማር	59,546,058.00	59,531,630.54	99.97%
2	ለተማሪዎች	18,400,000	18,399,999.18	99.99%
3	ለጥናትና ምርምር አገልግሎት	5,000,000.00	4,988,055.06	99.76%
4	ለማህበረሰብ አገልግሎት	2,000,000.00	1,999,935.93	99.99%
ድምር		169,894,400.00	169,856,379.08	99.98%

የውስጥ ገቢም 2,000,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 3,143,869.92 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸምም ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ 157.19% ሲሆን ገቢው የተሰበሰበውም

ከተከታታይ ተማሪዎች ነው። የመንግስት ኃብትና ንብረት በውስጥና በውጭ አዲተሮች ተመርምሯል። የመንግስት ኃብትና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን የሚያረጋግጥ የአዲት ምርመራ ተደርጎ በተገኙ የአሠራር ግድፈቶች ላይ የሙያ እና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል። የተማሪዎች ምግብ ቤት የንብረት አጠቃቀም እና አመዘጋገብ፣ የክሊኒክ የመድኃኒት አጠቃቀም አዲት ተደርጎ በተገኙ የአሠራር ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃዎች ተወስደዋል።

1.7. ቤተ-መጽሐፍትና ስነዳ

የዲጅታል ቤተ-መጽሐፍት በ50 ኮምፒዩተሮች የተደራጀ ሲሆን ተጨማሪ 50 ኮምዩተሮች እንዲገቡ ተደርጓል። ቤተ-መጽሐፍቱ የዋይፋይና ኢንተርኔት አገልግሎት እንዲኖረው ተደርጓል። የዩኒቨርሲቲው ቤተ-መጽሀፍት የ24 ሰዓት የተሟላ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን ከመጽሐፍት አደረጃጀትና ከንጽህና አንፃር የተሻለ ቁመና ላይ ይገኛል። በግዥ ማግኘት ያልተቻሉ መጻሕፍት ከፖሊፔዳ ኢንተርፕራይዝ ጋር ውል በመፈጸም መጽሐፍቶች ታትመዋል። በግዥ የመጡ መጽሐፍትን የካታሎጊንግ ሥራ ተሰርቶላቸው ለንባብ ዝግጁ ሆነዋል። መምህራን የሚያዘጋጇቸው አጋዥ ሞጁሎች ከማጣቀሻ መጽሐፍት ጋር አገልግሎት እየሰጡ ነው። በቁጥር አነስተኛ የሆኑ መጽሐፍትን ለሁሉም ተጠቃሚዎች ለማድረስ በሰዓት በመከፋፈል አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል። መጽሔቶች እና ጋዜጦች ተገዝተው ወደ ቤተ መጽሐፍት የገቡ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ለሚገኙ የተለያዩ ቢሮዎች የማሰራጨት ሥራም ተሰርቷል። ቤተ-መጽሐፍቱ የካይዘንን ፍልስፍና ተግባራዊ አድርጓል። የአካል ጉዳተኞች የማንበቢያ ክፍል ተለይቶ ተዘጋጅቷል።

1.8. የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት

በሁለተኛው ዙር ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል ሦስት ባለ አራት ፎቅ፣ ሦስት ጊዜያዊ ዶርሚተሪና አንድ ለላውንደሪ አገልግሎት የሚውል ሕንፃ በ105,507,756 ብር በ4 ተቋራጮች ተገንብቷል። የህንጻ ተቋራጮች የ300 ቀናት ኮንትራት የወሰዱ ሲሆን የመሰረተ ልማት ተቋራጮች ደግሞ በ2 ዓመት ከሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ ነው ኮንትራት የወሰዱት። የ3ቱ ባለ አራት ፎቅ የመኝታ አገልግሎት ሕንጻ ግንባታ አፈጻጸም 99.76% ላይ ሲሆን የላውንደሪ፣ የተማሪዎች ጊዜያዊ ማደሪያ ህንጻና የሁለት ባህላዊ ማብሰያ ቤቶች ግንባታም ተጠናቋል።

የውኃ፣ የመብራት፣ የስልክና የኢንተርኔት አቅርቦት፡- የውኃ መስመሩ 100% አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን እንዳይቋረጥም በውኃ አቅርቦትና ፍሳሽ ሠራተኞች ክትትል እየተደረገ 24 ሠዓት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የውኃ አቅርቦቱን ለማሳደግ ተጨማሪ የውኃ ፓምፕም ተዘጋጅቷል፡፡ መብራት በሁሉም ሕንጻዎችና በዋና መንገዱ ላይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ መብራት በሚጠፋበት ወቅትም ጀነሬተሮችን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲው መማር ማስተማርና ሌሎች ተግባራት ሳይቋረጡ ቀጥለዋል፡፡ ዘጠኝ ህንጻዎች ጀነሬተር ተገጥሞላቸዋል፡፡ በኮንትራክተር የሚሠራው የመብራት ግንባታ በ52,887,556.74 ብር የሚገነባ ሲሆን አፈጻጸሙ ያለበት ደረጃ 78.7% ላይ ነው፡፡ ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎትም እየተሰጠ ይገኛል፡፡

1.9. መንገድ

በዩኒቨርሲቲው ግቢ 9.701 ኪ.ሜ ዋና መንገድ በ66,260,280 ብር ለመገንባት በተቋራጭ ውል ተይዞ የዲች ሥራ፣ ጠጠርና አስፓልት በመሙላት ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈጻጸሙም 156.15% ላይ ነው፡፡ የውስጥ ለውስጥ የእግረኛ መንገድ 3.60 ኪ.ሜ በ34,958,964 ብር ለመገንባት ታቅዶ የጠጠርና ኮብል ስቶን ሙሌት እየተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙም 34.72% ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ የአፈጻጸም ደረጃዎች የተለኩት ሥራው ከሚጠይቀው የበጀት መጠን ጋር ሲሆን ይህም ሥራው ያለበትን ደረጃ በቀጥታ የሚነግረን ነው፡፡

1.10. የግቢ ውበት፣ ጽዳት፣ ትራንስፖርትና ደህንነት

የዩኒቨርሲቲውን ግቢ በአትክልት በማስዋብ ጽዱና አረንጓዴ የማድረግ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ አረንጓዴ ለማልበስ በዕቅድ የተያዘው ቦታ ጠቅላላ ስፋት 60,000 ካሬ ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 52,115 ካሬ ሜትር (86.85%) የሚሆነው በአረንጓዴ ተሸፍኗል፡፡ በዚህም ሳርና የአበባ ተክሎችን የመትከል፣ የማጨድ /የመከርከም/፣ ውኃ የማጠጣትና ተጨማሪ እንክብካቤዎችን የማድረግ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም በዚህ የበጀት ዓመት ብቻ 9,000 ችግኞች ተተክለው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ በችግኝ ተከላው ላይ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ሌሎች አካላት ተሳትፈውበታል፡፡ የእንሰሳት ሳይንስ፣ የዕፅዋት ሳይንስ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የተፈጥሮ ኃብት አያያዝ ሰርቶ ማሳያ (ሞዴል) ችግኝ ጣቢያ ተሰርቷል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሰባት (7) የመንግስት ተሸከርካሪዎች ያሉ ሲሆን የተሸከርካሪ እጥረትን ለመቅረፍ ሦስት (3) መኪኖችን በመከራየት አገልግሎት እየሰጡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አንድ ሚኒባስ በኪራይ በቀንና በማታ ለክሊኒኩ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን ሁለት (2) አውቶቢሶችን ተከራይቷል፡፡

በአውትሶርስ ሰራተኝነት ያሉት የካምፓስ ፖሊሶች የግቢውን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርገዋል፡፡ ሰላም እና ጸጥታን ለማስጠበቅ የተማሪዎች ህብረትን ጨምሮ ያሉ ልዩ ልዩ የተማሪዎች አደረጃጀት እና መላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

1.11. የተማሪዎች እንቅስቃሴ

በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተማሪዎች እንደየዝንባሌያቸው በንቃት የሚሳተፏቸው የተለያዩ አሥር ክበባት አለ፡፡ እነዚህም የሥነ-ውበት፣ የበጎ አድራጎት፣ የፀረ-ኤድስ፣ የሥርዓተ-ፆታ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የሥነ-ምግባር፣ የሠላም ፎረም፣ የአገርህን ዕወቅ፣ የስፖርት እና የተማሪ ፖሊስ ናቸው፡፡ የክበባት አመራሮች የክበባት፣ ማህበራትና በጎ አድራጎት ዘርፍ ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ ተደርጓል፤

ተማሪዎች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ቅርርብና መልካም ወዳጅነት ተማሪዎቹንም ሆነ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊያስመሰግናቸው የሚገባ መልካም ተግባር ሆኖ አልፏል፡፡

የተማሪዎች ህብረት ጠንካራ አደረጃጀት ያለው በመሆኑ ተማሪዎች በየጊዜው የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ለዩኒቨርሲቲው አመራር በማቅረብ እንዲፈቱ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህም ዓመቱን ሙሉ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡

የተማሪዎች ህብረት በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

- የተማሪ ፖሊሶች ቀጠናና ቀን በመከፋፈልና የተማሪዎችን አዳርና ውሎ በመጎብኘት የዩኒቨርሲቲውንና የተማሪዎችን ደህንነት መከታተል፣ መረጃ ማሰባሰብና ለሚመለከተው አካል ወጥነት ያለው መረጃ የመስጠት ስራ ተሠርቷል፤

- የሥነ-ምግባር ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት የምክር አገልግሎት ተሠጥተዋል፤
- የኢንተር ዲፓርትመንት እግር ኳስ ስፖርታዊ ውድድር እንዲካሄዱ ተደርጓል፤ የተሻለ አፈፃፀም ላሳዩ ትምህርት ክፍሎች፣ ተጫዋቾችና ዳኞች ተሰጥቷል፤
- ከደ/ማርቆስ እና ከደባርቅ ዩኒቨርሲቲዎች የተማሪ እግር ኳስ ክለብ ጋር የደርሶ መልስ የወዳጅነት ጨዋታ ተደርጓል፤
- በቤተ-መጻሕፍት ላይ በየተራ በመመዳደብ ዓይነት ችግር እንዳይኖር ከአስነባቢዎች ጋር በቅንጅት ተሠርቷል፤
- ከኢትዮጵያ ደም ባንክ ጋር በመተባበር ከበጎ ፈቃደኛ ተማሪዎች የሁለት ቀናት የደም ማሰባሰብ ሥራ ተሠርቷል፤

1.12. የዕቅድ አፈጻጸም ንጽጽር

ሰንጠረዥ 13፡ የ2011 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት የዕቅድ ክንውን ንጽጽር

ዕይታ	ተቋማዊ ግቦች	የአፈፃፀም መለኪያዎች	የ2011 ዓ.ም ዒላማ	ዓመታዊ ክንውን	በመቶኛ	ምርመራ
ደንበኛ (20%)	የዩቨርሲቲውን ገፅታ መገንባት	የማስተዋወቅ ሥራ ብዛት በቁጥር				
		በህትመት ሚዲያ	4	3	75%	1 ተጨማሪ መጽሔት 75% የተከናወነ
		ኢሌክትሮኒክስ ሚዲያ	2	9	450%	በቴሌቪዥን 6፣ በሬዲዮ 3
		መድረኮች	2	10	500%	
	የደንበኛና አጋር አካላትን እርካታ ማሻሻል	የደንበኞች እርካታ በመቶኛ	73	72.3	99.04%	
		የአጋር አካላት እርካታ በመቶኛ	70	-	-	
		የቅሬታ መጠን በመቶኛ	2.5	0	-	በአገልግሎት ዙሩያ ክፍተቶች ሲያጋጥሙ በፍጥነት ይስተካከላሉ፡፡
	ደንበኛና አጋር አካላትን ቁጥር ማሳደግ	የተማሪዎች ዲሲፕሊን ግድፈት በመቶኛ	0	1.5	-	37 የዲሲፕሊን ኬዝ
		መጠነ ማቋረጥ በመቶኛ	2	5.9	295%	127 ድሮፓውት እና 21 ዊዝድሮዋል
		መጠነ ስንብት በመቶኛ	4	4.2	105%	106 ተማሪዎች
		የተማሪዎች ብዛት በቁጥር				
		አዲስ መደበኛ ተማሪ በቁጥር	1500	1,455	95%	
		ተከታታይ	1000	1,806	180.6%	– እየተማሩ ያሉት 1163 ናቸው – የክረምት ትምህርትን አያካትትም
		የተሰጠ የማህበረሰብ አገልግሎት ብዛት በቁጥር	10	11	110%	
		የማህበረሰብ አገልግሎት ያገኙ ብዛት በቁጥር	1000	396	39.6%	በተጨማሪም ቁጥሩ ያልተካተተ አንድ የተፋሰስ እርከን ሥራ ተሰርቷል፤
		የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስርፀት ብዛት በቁጥር	1	2	200%	– Integrated Seed Sectors Development

						– Kossoye Development Project
		የጸደቀ የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል በቁጥር	24	25	104.2%	
		በታወቁ ጆርናሎች የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ማሳታም በቁጥር	4	37	925%	
		አጋር አካላት በቁጥር				
		የሀገር ውስጥ	3	1	33.33%	በ2010 ከነበሩት 1 ጨምሯል፡፡
		የውጭ ሀገር	2	2	100%	– Academic without Boarder – USAID
ፋይናንስ (10%)	የሀብትና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ	የበጀት አጠቃቀም በመቶኛ	100	99.98	99.98%	
		በአግባቡ ተይዞ ጥቅም ላይ የዋለ ንብረት በመቶ	80	95	118.75%	
		የካይዘን ፍልስፍናን ተግባራዊ ያደረጉ የሥራ ክፍሎች ብዛት በመቶኛ	70	50	71.43%	
	የውስጥ ገቢን ማሳደግ	የገቢ መጠን በብር	2,000,000	3,143,869.92	157.2%	ከተከታታይ ትምህርት የተገኘ ነው፡፡
የውስጥ አሰራር (40%)	የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል	የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተከናወነ ተቋማዊ ግምገማ ብዛት በቁጥር	1	1	100%	በትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት የተደረገ ጠቅላላ ግምገማ ነው፡፡
		የካሪኩለም ትውውቅ ያካሄዱ የትምህርት ክፍሎች ብዛት በቁጥር	24	24	100%	ሁሉም ትምህርት ክፍሎች
		የሥራ አፈጻፀም ግምገማ ያደረጉ የሥራ ክፍሎች በቁጥር	41	41	100%	ሁሉም የሥራ ክፍሎች
		አገልግሎታቸውን በስታንዳርድ አስደግፈው የሚሰጡ የሥራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	41	41	100%	ሁሉም የሥራ ክፍሎች
		የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ሰነድ በቁጥር	2	-	-	የፌዴራል ሠራተኞች የቅሬታ መመሪያን በመጠቀም ላይ ስለምንገኝ ተጨማሪ ማዘጋጀት አላስፈለገም፡፡
		የተፈቱ ቅሬታዎች በመቶኛ	100	100	100%	በዓመቱ ውስጥ 8 ቅሬታዎች ከተቋሙ ሠራተኞች ቀርበው ሁሉም ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡
		የማበረታቻ ሥርዓት ሰነድ በቁጥር	2	-	-	በሂደት ላይ ያለ

		ማበረታቻ የተደረገላቸው ሰራተኞች ብዛት በቁጥር	34	-	-	የምስክር ወረቀቶች ተሰጥተዋል
	የውስጥ ተግባቦትን ማጎልበት	ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተፈጠሩ የውይይት መድረኮች በቁጥር	2	2	100%	በዓመቱ መጀመሪያ እና በ1ኛው ሰሚስተር መጨረሻ ላይ የተደረገ
		በዩኒቨርሲቲው ካውንስል የተካሄዱ መድረኮች	4	2	50%	
		በዓመቱ በቦርድ የተከናወኑ የዕቅድ አፈፃጸም ግምገማዎች በቁጥር	4	2	50%	
		የውጤት ተኮር ሥርዓት የተገበሩ ሥራ ክፍሎች በቁጥር	41	41	100%	
		የትምህርትና ቴክኖሎጂ ልማት ሠራዊት ተግባራዊ የተደረገባቸው የሥራ ክፍሎች በቁጥር	41	41	100%	
		ዓመታዊ ስታትስቲካዊ መረጃ መጽሔት (Bulletin) በቁጥር	1	-	-	ዝግጅቱ ተጀምሯል
	የባለ-ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነትን ማሻሻል	ለሴት መምህራን የተዘጋጀ ሥልጠና ብዛት በቁጥር	3	2	66.7%	– ለ36 መምህራን “የአመራር ጥበብ” – ለ12 ሠራተኞች “ጥናትና ምርምር”
		ለሴት የአስተዳደር ሠራተኞች የተዘጋጀ ስልጠና ብዛት በቁጥር	2	1	50%	
		ለሴት ተማሪዎች የተዘጋጀ ስልጠና ብዛት በቁጥር	3	1	33.33%	ለ471 ተማሪዎች የህይወት ክህሎት
		ልዩ ዕገዛ የተደረገላቸው ሴት ተማሪዎች በመቶኛ	50	100	200%	
		ዕገዛ የተደረገላቸው የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በመቶኛ	60	100	166.7%	የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች 7 ናቸው፡፡
		የሴቶች የአመራር ተሳትፎ በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ በመቶኛ	15	3.4	22.7%	
መ ማ ማ	የሰው ኃብትን አቅም ማሳደግ	የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር በሬሾ (የመጀመሪ ዲግሪ፡ 2ኛ ዲግሪ፡ 3ኛ ዲግሪ)	1.5፡97፡1.5	4.7፡93.3፡1.5	-	
		ለ3ኛ ዲግሪ ትምህርት የሚሄዱ በቁጥር	4	4	100%	ሦስቱ በሂደት ላይ ሲሆኑ ከየትምህርት ክፍሉ ሁለት ሁለት መምህራን እንዲማሩ ተመልምለዋል፡፡

ርናዕድገት (30%)		የከፍተኛ ትምህርት የማስተማር ሥነ-ዘዴ (HDP) ስልጠና የወሰዱ መምህራን በቁጥር	30	17	-	እነዚህ ቀድመው የሰለጠኑ ናቸው፡፡
		የመምህር-ተማሪ ጥምርታ	1፡13	1፡12	-	መደበኛ
		የቴክኒካል ረዳቶች ብዛት በቁጥር	13	13	100%	2010 የነበሩ
		አዲስ የተቀጠሩ የአስተዳደር ሰራተኞች ብዛት በቁጥር	60	68	113.33%	
		ለአስተዳደር ሰራተኛ የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና ብዛት በቁጥር	6	6	100%	
		ለመምህራን የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና ብዛት በቁጥር	7	8	114.3%	
		የልምድ ልውውጥ ያገኙ የአስተዳደር ሠራተኞችና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ብዛት በቁጥር	70	80	114.3%	
	የቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ሽግግርን ማጎልበት	አውቶሜት የተደረጉ የሥራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	2	-	-	
		በዲጅታል ላይበራሪ የተደራጁ ኮምፒውተሮች ከተማሪ ብዛት አንጻር ያለው ጥምርታ	1፡40	1፡23	-	የተደራጁ 50 ኮምፒውተሮች ያሉ ሲሆን ተጨማሪ 50 ኮምፒውተሮችም ገብተዋል፡፡
		ሞዴል (በአይሲቲ የታገዙ) እና ዘመናዊና ተገቢነት ያላቸው መማሪያ ክፍሎች በመቶኛ	100	100	100%	
	ፋሲሊቲ በዓይነትና በብዛት ማሳደግ	የተሟላ ላቦራቶሪዎች ያሏቸው አካዳሚክ ክፍሎች በቁጥር	20	6	30%	እነዚህ የተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ እና የግብርና ምግብና አየር ንብረት ኮሌጅ ናቸው፡፡
		ዋና የማጣቀሻ መጽሐፍት-ተማሪ ጥምርታ	1፡15	1:12	-	
		የመማሪያ ክፍል-ተማሪ ጥምርታ	1፡60	1፡45	-	ለመደበኛ ተማሪዎች
		የዶርም-ተማሪ ጥምርታ	1፡4	1፡5	-	ግንባታ በመዘግየቱ
		የዋና መንገድ ግንባታ በመቶኛ	-	156.15	-	2 ዓመት ከ3 ወር ከሚወስድ ጠቅላላ ኮንትራት ውስጥ በበጀት አጠቃቀም የተለካ ነው፡፡
		የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ በመቶኛ	-	34.72	-	
		ኤሌክትሪክ ዝርጋታ በመቶኛ	-	78.7	-	
		ሳኔቴሪ በመቶኛ	-	85.92	-	

		ሦስት የተማሪ ማደሪያ ጊዜያዊ ሕንጻ ግንባታ በመቶኛ	-	100	-	
		ሦስት የተማሪዎች ቋሚ ማደሪያ ሕንጻ ግንባታ በመቶኛ	-	99.76	-	ከ300 ቀናት ውል 99.76 በመቶ የተከናወነ
		አንድ የተማሪዎች መማሪያ ክፍል ሕንጻ ግንባታ በመቶኛ	-	19.91	-	ከ300 ቀናት ውል ውስጥ
		አንድ ላውንደሪ ግንባታ በመቶኛ	-	100	-	
		ሁለት ባህላዊ ማብሰያ ቤቶች በቁጥር	-	100	-	
		ጀኔሬተር የተዳረሰባቸው ህንጻዎች ብዛት በቁጥር	10	9	90%	
		የስልክ መስመር በቁጥር	40	-	-	ለኃላፊዎች የካርድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
		የግቢ ዙሪያ አጥር በሽቦ በመቶኛ	100	-	-	ባለፈው ዓመት በህብረተሰቡ ተሳትፎ 2.6 ኪ.ሜ ታጥሯል፡፡
		ጽዱና አረንጓዴ ግቢ በመቶኛ	25	86.85	347.4%	ተጨማሪ ችግኞች እየተተከሉ ነው፡፡
		ስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት በመቶኛ	50	-	-	እጅግ አመርቂ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡
	የሠራተኞችን እርካታ መጨመር	የረኩ ሠራተኞች በመቶኛ	70	74.3	106%	የእርካታ አሰስመንት ጥናት ተካሂዶ
	አሠራርና አደረጃጀትን ማሻሻል	አዲስ የተዘጋጁ የአፈጻጸም መመሪያዎች ብዛት በቁጥር	7	8	114.3%	
		የተሻሻሉ መመሪያዎች ብዛት በቁጥር	2	-	-	
		የተሻሻሉ የሥራ መደቦች ብዛት በቁጥር	10	30	300%	
		አዳዲስ የተፈጠሩ የሥራ መደቦች ብዛት በቁጥር	41	40	97.6%	
		የ1ለ5 መመሪያን ተግባራዊ ያደረጉ ቡድኖች በመቶኛ	70	75.6	108%	ከ41 የሥራ ክፍሎች ውስጥ 31ዱ ተግባራዊ አድርገዋል፡፡
	መረጃ አያያዝና አስተዳደርን ማሻሻል	በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ የሚጠቀሙ የሥራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	2	-	-	

ክፍል ሦስት፡ የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች

7.1. አጠቃላይ ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ግቦችንና ዋና ዋና ተግባራትን የአፈጻጸም ስኬት ለመለካት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሂደቱ ላይ ችግሮች የሚፈጥሩ ጉዳዮችን የመለየትና በየጊዜው የመፍትሔ አቅጣጫ የማስቀመጥ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድም ሆነ በየደረጃው ያለው አመራር ግምገማዎችን በማድረግ የዩኒቨርሲቲው ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እያደረጉ ናቸው፡፡

የግንባታና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በትምህርት ሚኒስቴር ሥር ቢሆኑም በበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት እንዲጠናቀቁ የክትትልና ግምገማ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ለተማሪዎች የሚደረግን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ መምህራን ዕቅድ ይዘው የቱቶሪያል ትምህርት እየሰጡ ናቸው፡፡ በሁሉም ትምህርት ክፍሎች ለሴት ተማሪዎች የቱቶሪያል ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የተከታታይ ምዘና በወቅቱ እየተሰጠ መሆኑን በየጊዜው ክትትል ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት እንዳይባክኑ፣ በተለያዩ ምክንያቶችም የሚባክኑ ከሆነ በወቅቱ እንዲካካሱ በትምህርት ጥራት ዳይሬክቶሬት በኩል ያላሰለሰ ጥረት ሲደረግ ቆይቶ ውጤትም አስገኝቷል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ እስካሁን ሁለት ጊዜ ተሰብስቧል፡፡ በመጀመሪያ ስብሰባው የዩኒቨርሲቲውን የ2010 ዓ.ም በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም፣ የሁለት ዓመታት ስትራቴጅያዊ ዕቅድ እና የ2011 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ ገምግሞ አጽድቋል፡፡ በሁለተኛው ስብሰባ ደግሞ የ2011 ዓ.ም በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገምግሞ አጽድቋል፡፡

7.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

7.2.1. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራ ጎኖች

- *በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ምንም ዓይነት የጸጥታ ችግር አለመከሰቱ፡-* በተለይም ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ወቅታዊ የፖለቲካና የጸጥታ ሁኔታ አንጻር ብዙ

ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ግጭቶች የተስተዋሉ ሲሆን እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ላይ ግን በተሠራው ጠንካራ ክትትልና ተከታታይ ሥራ ምክንያት ተመሳሳይ ድርጊት አልተከሰተም፡፡

- *ምሁራን ለዩኒቨርሲቲው መምህራን ሥልጠና መስጠታቸው፡-* በዓለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ ባሉ የምርምር ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ ተመራማሪነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ምሁራንን በመጋበዝ የምርምር ወረቀቶች እንዲያቀርቡና ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሥልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡
- *ጠንካራ የተማሪዎች ህብረት መኖሩ፡-* የተለያዩ ግብዓቶችን ፈጥኖ በማሟላት እና ከተማሪ ተወካዮች ጋር ተከታታይ ውይይት በማድረግ ችግሮች በወቅቱ እየተፈቱ መማር ማስተማሩ በተሳካ ሁኔታ ቀጥሏል፤ የዚህ አንዱ ምክንያትም የተማሪዎች ህብረት ጠንካራ በመሆኑ ነው፡፡
- *ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መዘጋጀቱ፡-* ዩኒቨርሲቲው የሁለት ዓመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድና ከዚያ የሚመነጭ የ2011 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የ2012 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድም እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡
- *ደማቅ የተማሪዎች አቀባበል፡-* በተማሪዎች አቀባበል ላይ ሁሉም የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡
- *ስፖርታዊ ውድድሮች መደረጋቸው፡-* በተማሪዎች መካከል ስፖርታዊ ውድድሮችን በማዘጋጀት በመካከላቸው ወንድማማችነት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡
- *ግቢውን አረንጓዴ የማድረግ ሂደት፡-* የዩኒቨርሲቲውን ግቢ ውበትና ንጽህና በተለይም ግቢውን አረንጓዴ የማልበስ ሥራ በአመርቂ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ አረንጓዴ እንዲሆን ከተያዘው የግቢው የቆዳ ስፋት ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ ተግባራዊ ሆኗል፡፡
- *የኢንተርኔት አገልግሎት መኖሩ፡-* ከዩኒቨርሲቲው አዲስነት ጋር ሲነጻጸር የኢንተርኔት አገልግሎት መጀመሩ እንደ ቀላል ነገር የሚታይ አይደለም፡፡
- *First Day First Class መርህ መተግበሩ:-* የመጀመሪያ ቀን የመጀመሪያ ክፍል በተሳካ ሁኔታ ተፈጽሟል፡፡

- *የተጀመረ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራ መኖሩ፡-* ተቋሙ አዲስ መሆኑ ሳይገድበው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በሜጋ ፕሮጀክት መርህ እየተሠራ ይገኛል፡፡

7.2.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ደካማ ጎኖች

- የኔትወርክ ዝርጋታ በተለያዩ የኔትወርክ ዕቃዎች እጥረት ምክንያት አለመጠናቀቁ፤
- የኬሚስትሪ፣ የፊዚክስ፣ የስፖርት ሳይንስ እና የሥነ-ህይወት ትምህርት ክፍል የኬሚካልና የአፓራተስ ግዥ መጓተት/መዘግየት
- የስፖርት ሜዳ ዝግጅት መዘግየቱ፤

7.3. ያጋጠሙ ችግሮች

- የ2ኛው ዙር ሕንጻ ግንባታ መዘግየቱ፤
- የእንጅባራ ቻግኒ የአስፓልት መንገድ እስከ ዩኒቨርሲቲው ወሰን ጫፍ ድረስ መንታ መንገድ ባለመሆኑ ምክንያት ለተማሪዎች እንቅስቃሴ ስጋት መፍጠሩ፤
- የግዥ መጓተት በመኖሩ የቢሮና የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት ላይ ውስንነት መኖሩ፤

7.4. የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች

- የተማሪዎች ማደሪያ ችግርን ለማቃለል ጊዜያዊ የተማሪዎች ማደሪያ እየተገባ ነው፡፡
- በማዕከላዊ መንግስት ቃል በተገባው መሠረት መንገዱ መንታ ሆኖ እንዲሠራ ለሚመለከታቸው አካላት ተደጋጋሚ የማሳወቅ ሥራና ክትትል እየተደረገ ነው፡፡

7.5. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ተደጋጋሚ የሆነ የመብራት መቆራረጥ፤
- የመምህራን መኖሪያ ቤት ጉዳይ፤
- የፕሮጀክት በጀትን ከማስተዳደር ጋር በተገናኘ የሚደርሰው ከፍተኛ የግንባታ መጓተት እና የተማከለ የፕሮጀክት የበጀት አስተዳደር መኖር፤
- የመንግስት የግዢ ሥርዓት የተንዛዛ መሆኑና አቅራቢዎችም በውላቸው መሠረት ያለመፈጸም ችግሮች መታየታቸው፤

- አርሶ አደሮች በዩኒቨርሲቲው መካከል መንገድ እንዲወጣላቸው በተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረባቸው፤
- ተነሺ አርሶ አደሮች ካሳ የተከፈላቸው ቢሆንም ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸው አመነሳታቸው፤
- ዩኒቨርሲቲው አጥር የሌለው መሆኑ፤

አባሪዎች

1) የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች

የዩኒቨርሲቲው ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች፣ ማስተወቂያዎችና ሌሎች መልዕክቶች በኦፊሴላዊ የፌስቦክ ገጽ /Facebook Page/ **ይተላለፋል፡፡**

የዩኒቨርሲቲው ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ /Website/



የዩኒቨርሲቲው ኦፊሴላዊ ዩቱዩብ /YouTube/



2) ልዩ ልዩ ፎቶዎች

አምባሳደር ሙሀመድ ድሪር ከዩኒቨርሲቲው ከፍተኛና መካከለኛ አመራር ጋር ትውውቅ ሲያደርጉ፤ ህዳር 16 ቀን 2011 ዓ.ም

ተማሪዎች የገና በዓልን ሲያከብሩ ‹የዞኑ አስተዳደር ኃላፊዎች በተገኙበት›፤ ታህሳስ 29 ቀን 2011 ዓ.ም

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ኃብትና ቴክኖሎጂ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ከተማሪዎች ህብረት አባላትና ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ውይይት ሲያደርጉ፤ ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ.ም

በትምህርት ክፍሎች መካከል የተደረገው የእግር ኳስ ውድድር ሲጀመር፤ ታህሳስ 6 ቀን 2011 ዓ.ም

ተማሪዎችና መምህራን በካናዳ አገር የዳልሀውሲ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ በሆኑት ፕሮፌሰር ተሰማ አስታጥቄ የቀረበውን ሴሚናር ሲከታተሉ፤ ህዳር 27 ቀን 2011 ዓ.ም

ፕሮፌሰር ኃብሩ ለመምህራንና ለተማሪዎች የሰጡት የማነቃቂያ ፕሮግራም

የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ለአዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች አቀባበልና ሲያደርግና በ2010 ዓ.ም ከፍተኛ ወጤት ያስመዘገቡ ሴት ተማሪዎች የእውቅና የምስክር ወረቀት ሲሰጥ፤ ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም

የአካባው ማህበረሰብ ተማሪዎችን ሲቀበል

የ2000 ችግኞች ተከላ ሀምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም

የአዊ ዣንጥላ (ድጋግ) ሥራ ሥልጠና

የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ከደብረማረቆስና ከደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር የእግር ኳስ ግጥሚያ